# <u>ጥናት አንድ ያዕ 1፡1-12 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. ጸሐፊው ያዕቆብ እንደሆነ፣ የተጻፈላቸው ደግሞ ለአስራ ሁለቱ ነገዶች መሆኑን እናነባለን፡፡ ጸሐፊው ራሱን የሚያስተዋውቀው የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ወይም አገልጋይ በማለት ነው፡፡
2. ዳን 2፡21 ጥበብ ከእግዚአብሄር እንደሚሰጥ፣ መዝ 111፡10 እግዚአብሄርን በመፍራት እንደሚጀመር፣ ምሳ 13፡20 ጠቢባን የሆኑ ሰዎችን በመስማት፣ መክ 7፡25 ልብ ብሎ ነገሮችን በመመርመርና በመማር ጥበብን ማግኘት እንደሚቻል እንገነዘባለን፡፡ ያዕ 1፡5 ላይ ያዕቆብ የተናገረው በዳን 2፡21 ላይ ካለው የሚለየው በሁለቱም ጥቅሶች ውስጥ ሰጪው እግዚአብሄር እንደሆነ ብናይም፤ በዳንኤል ላይ ለጥበበኛ እንደሚሰጥ ሲሆን፣ በያዕ 1፡5 ላይ ግን ጥበብ እንደጎደለው ለተረዳና እግዚአብሄርን ለሚጠይቅ ሰው ነው የሚሰጠው፡፡
3. በዚህ ቁጥር ውስጥ ስለ እግዚአብሄር ጥበብ አሰጣጥ የተነገሩት አራት ነገሮች፤ የሚሰጠው እንደሌላቸው አውቀው ለሚለምኑት ነው፣ ሳይነቅፍ ነው የሚሰጠው፣ አሰጣጡ በልግስና ነው፣ የሚሰጠውም ለጠየቀው ሁሉ ነው፡፡
4. ስለተቀባዩ ሰው ይህ ክፍል የሚነግረን ዋነኛ ነገር፤ ለማኙ ሳይጠራጠር በእምነት እንዲለምን ነው፡፡ ተጠራጣሪን ሰው ጸሐፊው የሚያነጻጽረው በነፋስ እንደሚገፋና እንደሚናወጥ የባህር ማዕበል ነው፡፡
5. ዝቅ ያለው በከፍታው፣ ባለጠጋም በውርደቱ እንዲመካ ያለበት ዋነኛ ምክንያት፤ ነገሮች ሁሉ ውበት፣ ሃብትና የመሳሰሉት አለኝ የምንላቸው ነገሮች ሁሉ ጊዜያዊና ሃላፊ፣ የሰው ልጅም ራሱ እንደ አበባና እንደ ሳር ረጋፊ መሆናቸውን በማስረዳት ነው፡፡
6. በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ያዕቆብ ለአንባቢዎቹ የሚሰጠው ምክር ልዩ ልዩ መከራ ሲገጥማቸው በሙሉ ደስታ እንዲቀበሉት በማለት ነው፡፡ ሊደርሱባቸው ስለሚችሉት የመከራ ዓይነቶች የተናገረው ‹‹ልዩ ልዩ›› በማለት ነው፡፡ ከነዚህም ጥቂቶቹን ለመዘርዘር ያህል…..
7. እንደነዚህ ያሉትን አነጋገሮች ማለቱ አይመስለኝም፤ ፀሐፊው ‹‹እንደ ሙሉ ደስታ ቁጠሩት›› ሲል ከመከራው በስተኋላ እግዚአብሄር በህይወታችን የሚሰራው ነገር እንዳለ በመረዳት መከራው የሚያስገኘውን መልካም ነገር በማሰብ ከልብ የመነጨ ደስታ እንድንለማመድ ማለቱ ነው፡፡
8. ይህ ምክር ለሁሉም አይደለም፤ ምክንያቱም በቁጥር 2 ላይ ያዕቆብ ምክሩን ‹‹ወንድሞች ሆይ›› በማለት የጀመረ መሆኑና፤ ከዚያም በተጨማሪ በቁ3 ላይ ደግሞ መከራው የሚያስገኘውን በረከት ‹‹ታውቃላችሁ›› በማለት የሚናገር ስለሆነ፤ ይህንን ዓይነቱ እግዚአብሄር በመከራ የሰውን ህይወት ይሰራል የሚለው እውቀት ሊገኝ የሚችለው በአማኞች ዘንድ ብቻ ነው ሊሆን የሚችለው፡፡ የእምነት መፈተን ትዕግስትን እንደሚያስገኝ ነው፡፡

## ጥናት ሁለት ያዕ 1፡13-27 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. እነዚህ ሁለት ክፍሎች የሚቃረኑ ሳይሆኑ ሁለቱም የተለያዩ ሃሳቦችን ያዘሉና በዓውደ ምንባቡ መሰረት መታየት የሚኖርባቸው ናቸው። ከቁ1 ጀምሮ ጸሐፊው የሚናገረው የፈተና ዓይነት አማኝን ለማሳደግና ክርስቶስን ወደ መምሰል ለማድረስ እግዚአብሄር የሚጠቀምበት ዓይነቱ ሲሆን፤ በ13-15 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ የምናነበው የፈተና ዓይነት ግን አማኝን ካለበት ሥፍራው ለማስለቀቅና ለመጣል የሚመጣ ከጠላት የሆነ ክፉ የፈተና ዓይነት ስለሆነ የዚያ ዓይነቱ ፈተና ከእግዚአብሄር ሊመጣ እንደማይችል ነው ያዕቆብ የሚናገረው።
2. የአብርሃምን በእግዚአብሄር መፈተን ከሁለተኛው ፈተና ውስጥ ነው የምመድበው፤ ዘፍ 22፡12 ላይ እግዚአብሄር የተናገረውን ስንመለከት አብርሃምን በእምነትና በመታዘዙ እንዲያድግ ለማድረግ እንጂ ከእርሱ ለመለየትና ለመጣል ያመጣው ፈተና እንዳልነበረ ያሳየናል። ለዚህ ዓይነቱ ፈተና ምንጭ አድርጎ የሚነግረን ሰው ራሱ በክፉ ምኞቱ ሲሳብና ሲታለል እንደሆነ ይነግረናል።
3. እግዚአብሄር ልጆቹን ለመጣል ክፉን ፈተና ወደ የሚልክ አባት ሳይሆን በጎ የሆነ ስጦታና በረከት የሆነ ነገር ሁሉ ከእርሱ ዘንድ እንደሚመጣ እንዲያውቁ ነው የሚያስተምራቸው። ይህ ‹‹አትታለሉ›› የሚለውን ሃሳብ ያዕቆብ የጨመረበት ምክንያት፤ ብዙ ጊዜ እኛ ሰዎች መከራን እንጂ በረከትንና በጎ ነገርን ከእግዚአብሄር ጋራ ከምናያይዝ ይልቅ የሰጠንን ወይም ያደረገልንን ሰው እንጂ ከእርሱ በስተኋላ ያለውን የእግዚአብሄር በጎነት ማየት ስለምንቸገር ነው።
4. የእግዚአብሄርን አለመለዋወጥ መናገር ያስፈለገው ምክንያት፤ ከላይ የተናገረውን ሃሳቡን ለማጠናከር ነው፤ ማለትም እርሱ ዛሬ ሊጥለንና ከእርሱ ሊለየን ክፉ ፈተና አምጥቶ ነገ ደግሞ በጎ ስጦታና በረከት የሚያፈስልን ሳይሆን ሁልጊዜ ሳይለዋወጥ ከመልካምነቱ የሚያጠግበን ነው ለማለት ነው። ለበጎ ስጦታና ፍጹም በረከት ምሳሌ ሆኖ የተጠቀሰው ነገር በቁ18 ላይ የምናየው በእውነት ቃል እንደወለደንና ልጆቹ ማድረጉ ነው።
5. አንባቢዎቹ እንዲያውቁና እንዲያስተውሉት የፈለገው እውነት ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ እንዲሆንና ለመናገርና እንዲሁም ለቁጣም የዘገየ እንዲሆን ነው። ለዚህ እውነት በምክንያትነት የነገራቸው ሃሳብ፤ የሰው ቁጣ የእግዚአብሄርን ጽድቅ እንደማያመጣ ነው።
6. የዚህ ዓይነቱ ሰው በመስተዋት ቆሻሻውን ተመልክቶ ነገር ግን ራሱን ሳያጸዳና ሳያስተካክል እንደቆሸሸ በሚሄድ ሰው ነው የሚመስለው፤ የዚህ ዓይነት ሰው ከቃሉ ሊመጣ የሚችለውን በረከት ተካፋይ የመሆን እድል አይኖረውም። ሶስቱ ባህርዮች ህጉን ተመልክቶ የሚጸና፣ የሰማውን የሚያደርግና ሌላው ደግሞ የማይረሳ ማለትም የተማረውን ደጋግሞ የሚያሰላስል ማለት ነው።
7. ቁ18 ላይ ‹‹በእውነት ቃል ወለደን›› በማለት ዳግም የተወለድነው በቃሉ እንደሆነ እናያለን፤ ቁ21 ነፍሳችንን ማዳን የሚችልና በውስጣችንም የተተከለ ነገር አድርጎ ይነግረናል፤ ቁ25 ላይ ደግሞ ነጻ የሚያወጣ ፍጹም ህግ እንደሆነ ተነግሮናል።
8. እነዚህ ሁለት ዘርፎች ሆነው የምናያቸው፤ አንደኛው በሌሎች ላይ ያተኮረ ማለትም እርዳታ የሚያስፈልጋቸው በዙሪያችን ያሉትን ሰዎች በችግራቸው መርዳት ሲሆን፤ ሌላኛው ደግሞ በራስ ህይወት ላይ ያተኮረ ማለትም በቅድስና መኖርና ከዓለም ርኩሰት ራስን መጠበቅ ናቸው።

# ጥናት ሶስት ያዕ 2፡1፡13 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ያዕቆብ በዚህ ክፍል የሚያስተላልፈው ትዕዛዝ በአጭሩ አድልዎ እንዳናደርግ ነው፡፡ ይህንን ትዕዛዝ እንዲቀበሉትና እንዲኖሩበት በያዕቆብ አዕምሮ ውስጥ ያሉት ሰዎች በክርስቶስ ኢየሱስ ያመኑትን እንደሆነ ከቁ1 መረዳት እንችላለን፤ በተጨማሪም ገና ሲጀምር ‹‹ወንድሞቼ ሆይ›› የሚለው አነጋገሩ ወደዚህ ሃሳብ ያመጣናል፡፡
2. በእነዚህ ክፍሎች ውስጥ እግዚአብሄር አምላካችን እርሱ የሰውን ፊት አይቶ የማያደላና ሁሉንም በእኩልነት የሚያይ አምላክ ስለሆነ፤ እኛም ልጆቹ ሆነን እርሱን የምንመስል ልንሆን ስለሚገባን፤ እንደ እርሱ ሰዎችን ሁሉ በእኩልነት ያለአድልዎ እንድንመለከት የሚያስተምረን ሃሳብ ነው፡፡
3. አንዱን ከሌላው አበላልጠን የምንመለከት ዓይነት ሰዎች ከሆንን፤ በክፉ ሃሳብ የተያዝን ፈራጆች እንደሆንን ያዕቆብ ይነግረናል፤ በዚህ ተቃራኒ ደግሞ ጌታ ኢየሱስን ለማጥፋት የሚከታተሉት ጠላቶቹ እንኳን በማቴ 22፡16 ከተናገሩት አነጋገር እንደምንረዳው እርሱ ለማንም የሰውን ፊት አይቶ እንደማያዳላና ሁሉንም በእኩልነት የሚያይ ጌታ እንደሆነ መስክረውለታል፡፡
4. ይህንን ሲል ተቃራኒ ሃሳብ ማምጣቱ አይደለም፤ ምክንያቱም እግዚአብሄር ድሆችን ስለድህነታቸው መንግሥቱን አያወርሳቸውም፤ ባለጠጎችንም ደግሞ ስለባለጠግነታቸው ከመንግሥቱ አይከለክላቸውም፡፡ ማቴ 19፡16-23 ላይ ስናነብ በባለጠጋውና በኢየሱስ መሃል በተካሄደው ውይይት ባለጠጋውን ከዘላለም ህይወት የከለከለው የነበረውን ንብረት ስለ ኢየሱስ መተው አለመፈለጉና የልቡ ሁኔታ እንጂ ባለጸጋ የመሆኑ ሁኔታ አልነበረም፡፡
5. በቁ5 ላይ ‹‹እግዚአብሄር›› በቁ6 ላይ ደግሞ ‹‹እናንተ ግን‹‹ እያለ በእግዚአብሔር አመለካከትና በክርስትያኖች አመለካከት መሃል ያለውን ልዩነት በማነጻጸር ነው የሚያስተምራቸው፡፡ እግዚአብሄር ድሆችን እንደመረጣቸው፤ እኛ ግን እንዳዋረድናቸው ነው የሚነግረን፡፡ ዛሬም ቢሆን አለባበስ፣ በዘር፣ በቋንቋ፣ በቀለምና በመሳሰሉት ሁሉ በቤተክርስትያን ውስጥ ትልቅ አድለዎና መለያየት እንደሚታይ የታወቀ ነው፡፡
6. አድልዎ ሳናደርግ ሰዎችን ሁሉ በእኩልነት ማየታችን በያዕቆብ አነጋገር ‹‹ባልንጀራህን እንደራስህ አድርገህ ውደድ›› የሚለውን ትዕዛዝ እንደጠበቅን አድርጎ ነው የሚነግረን፡፡ ያዕቆብ አድልዎ ማድረግን ወይም በሰዎች መሃል ልዩነት ማሳየትን በቀጥታ ሃጥያትና ህግ ተላላፊነት እንደሆነ በቁ9 ላይ ይናገራል፡፡
7. በጌታ ፊት ሊያስፈርዱብን የሚችሉት ሁለት ነገሮች የምናደርጋቸው ድርጊቶችና፣ የምንናገራቸው ቃላት ናቸው፡፡ በክርስቶስ ያመነ ሰው እውነትም ኩነኔ አያገኘውም፤ ነገር ግን አማኝ ሁሉ በምድር ጌታ በሰጠው ዘመኑ በሚሰራውም ሆነ በሚናገረው ነገር መልስ ለመስጠት በጌታ ፊት እንደሚቀርብ በ2ኛ ቆሮ 5፡10 ላይ ይነግረናል፡፡
8. ያዕቆብ የሚመክረን በዘፈቀደ የፈለግነውን እየተናገርንና የመሰለንን ሁሉ እያደረግን የምንመላለስ ሰዎች ሳንሆን፤ የምንናገረውና የምንሰራው ነገር በተለይም አድልዎን በተመለከተ ፍርድ የሚያስፈርድብን ነገር እንደሆነ እያሰብን እንድንኖር ነው፡፡

# ጥናት አራት ያዕ 2፡14-26 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ሊያድን የሚችል ትክክለኛ የሚባለው እምነት ሥራ የሚሰራ ሲሆን ነው። በያዕቆብ አነጋገር የራሳችንን ህይወት ለመመዘን ከፈለግን ልንጠይቅ የሚገባን ጥያቄ፤ እምነቴ በሥራ እየተገለጠ ነው ወይ? ብለን መጠየቅ መልካም ነው።
2. በአማኞች መሃል ድሆች ወይም ችግረኞች ሊኖሩ ይችላሉ፣ ወንድሞቻችንና እህቶቻችንን በችግራቸው መርዳት ከእኛ ከአማኞች ይጠበቃል፣ የተቸገሩትን ወገኖቻችንን መርዳታችን የሚያድነን ነገር ባይሆንም የመዳናችን ወይም የማመናችን ማረጋገጫ ነው። እምነታችን እኛን ራሳችንን ከመጥቀም አልፎ በአካባቢያችን የሚገኙትን ሰዎች ጭምር የሚጠቅም ሊሆን እንደሚገባው ይህ ክፍል ያስተምረናል።
3. አዎን ሰው እምነት ኖሮት ሥራ ግን ላይኖረው ይችላል፤ ይህንንም ማለት የሚያስችለኝ ያዕቆብ እንደዚህ ዓይነት እምነት የለም ሳይሆን እያለን ያለው በቁ26 ላይ መንፈስና ሥጋን፣ ከእምነትና ሥራ ጋራ በማነጻጸር የተናገረው አነጋገር እምነቱ አለ ነገር ግን ህይወት ስለሌለበት በድን ወይም ምውት ነው ነው የሚለን። እኛ እግዚአብሄር እንዳለ በእውቀት ደረጃ ብቻ የተቀበልን ሳንሆን ቃሉ የሚለንን ለመታዘዝም ልባችንን ያዘጋጀን ስንሆን፤ ሰይጣን ግን በእውቀት ላይ ብቻ የተመሰረተ እምነት ነው ያለው።
4. በዚህ ክፍል ያዕቆብ በነቀፋ እየተናገረ ያለው እምነት ያለ ሥራ ሊኖር ይችላል ብሎ የሚያምነውን ሰው እንደሆነ ከዚያው ቁ20 ላይ እናነባለን። ጸሐፊው የእምነትን ዋጋ ቢስነት እያረጋገጠ ሳይሆን፤ እምነት ብቻውን ያለ ሥራ የማይጠቅም ነገር እንደሆነ ሊያስረግጥ ነው።
5. የመጀመሪያው ማስረጃ አብርሃም ሲሆን፤ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ምስክር ሆና የቀረበችው ጋለሞታይቱ ረዓብ ናት። እኔ እንደሚመስለኝ ከሆነ አብርሃም አብዛኛውን ህይወቱን እግዚአብሄርን በመታዘዝ የእግዚአብሄር ወዳጅ የሚል ስም ያተረፈ ሰው ብዙዎች እሱ የደረሰበት እደርሳለሁ ብለው ስለማያምኑ፤ ረዓብ ደግሞ አብዛኛው የእድሜ ዘመኗ በአሳፋሪ ህይወት ስለኖረች እርሷ በእምነት ከኖረች እኔም ልኖር እችላለሁ ለማለት ስለሚያስችል ይመስለኛል።
6. እኔ በሁለቱ ጸሐፊዎች መሃል ቅራኔን አላይም፤ ጳውሎስ በእግዚአብሄር ፊት የሚጸደቀው ምንም ዓይነት ሥራ ሳይጨመርበት በእምነት እንደሆነ ለማረጋገጥ የተናገረው ሲሆን፤ በሌላ በኩል ያዕቆብ ደግሞ በሰው ፊት የእምነት ትክክለኛነት ሊረጋገጥ የሚችልበትን መንገድ ለማስረዳት ሲሆን፤ ይኸውም አምናለሁ ብሎ በማለት ብቻ ማረጋገጥ እንደማይቻልና ያለ ሥራ እንደማይሆን ይናገራል። ዋና መታየት የሚኖርበት ነገር ጳውሎስ በእግዚአብሄር ፊት መጽደቅ ላይ ሲያተኩር ያዕቆብ ደግሞ ዓውደ ምንባቡን ሰፋ አድርገን ስንመለከት በሰው ፊት በመጽደቅ ላይ ነው ትኩረታቸው።
7. በማድረግ እንደሚመጣ ሆኖ ያየነው ሃጥያት፡ አድልዎ ማድረግን ሲመለከት፤ ባለማድረግ ምክንያት ሃጥያት የሚሆንብን ነገር ደግሞ የተራቡና የተቸገሩትን አለመርዳት ነው።

# ጥናት አምስት ያዕ 3፡1-18 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ለአንባቢዎቹ በዚህ ቁጥር ላይ እየሰጠ ያለው ምክር ብዙዎቻቸው የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪ እንዳይሆኑ ነው፤ ምክንያቱም ሰዎችን ከሚያስተምር ሰው ብዙ እንደሚጠበቅና ባስተማሪ ላይ ፍርዱ እንደሚብስ ነው የሚናገረው፡፡ ያዕቆብ በዚህ ቁጥር ላይ ስለራሱ ተጨማሪ ነገር የነገረን እርሱ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪ እንደሆነ ነው፡፡
2. አስተማሪዎችን ተስፋ ለማስቆረጥ ሳይሆን ከአስተማሪነት ጋራ የሚመጣውን ትልቅ ሃላፊነት ተረድተው እንዲገቡበት ነው፡፡
3. ፈረስን የሚገዛ ትንሽ ልጓም ፣ የመርከብን አቅጣጫ የሚቀይር ትንሽ መሪና ትልቅ ጫካን ማቃጠል የሚችል ትንሽ እሳት ናቸው፡፡ እነዚህን ምሳሌዎች በመጠቀም ያዕቆብ ማስተላለፍ የፈለገው እውነት፤ እነዚህ ሶስት ነገሮች ምንም እንኳን ትንሽ ሆነው በሰው አይን ቢታዩም የሚያደርጉት በጎ ነገርም ሆነ ክፋት እጅግ ትልቅ እንደሆነ፤ እንዲሁም የሰው ምላስ ትንሽ መስላ ብትታይም እንኳን ልታደርግ የምትችለው ነገር እጅግ ታላቅ እንደሆነ ለማስገንዘብ ነው፡፡
4. ከምላስ ጋራ ለማነጻጸር የተጠቀመው እንስሶችን፣ አዕዋፍን፣ በምድር የሚሳቡና በባህር የሚኖሩ ፍጥረታትን ነው፡፡ ስለምላስ ያዕቆብ የደረሰበት ድምዳሜ ሰው እነዚህን ነገሮች ሁሉ መግራት ችሏል፤ ነገር ግን ማንም ሰው ምላሱን መግራት እንደማይችል ነው፡፡
5. እነዚህ ሶስት ነገሮች አንዱ፡ ከአንድ ምንጭ ጣፋጭና መራራ ውሃ ሊመነጭ አይችልም፤ ሁለተኛው፡ ከበለስ ወይራ ወይም ከወይራ በለስ ሊፈራ እንደማይችልና፣ ሶስተኛው ደግሞ ከጨው ውሃ ጣፋጭ ውሃ ሊገኝ እንደማይችል ነው፡፡ እነዚህን ነገሮች ማንሳትና መናገር ያስፈለገው ምክንያት አማኞች በምላሳቸው ሲያደርጉት ስለሚሰሙት ነገር ከተፈጥሮ እንዲማሩ ለማድረግ ነው፡፡
6. ክርስትያኖችን ያዕቆብ የሚያዘው ከአንደበታቸው በረከትና መርገም እንዳያወጡ ወይም ምላሳቸውን እንዲገሩ ነው፡፡ እኔ እንደሚገባኝ ከሆነ በቁ7-8 ያለው ክፍል የሚናገረው ሰው ለተባለ ሁሉ ማንኛውም ሰው ምላሱን መግራት እንደማይችል የሚናገር እውነት ሲሆን በቁ9-12 ያለው ክፍል ደግሞ የሚናገረው ጌታን ለሚያውቁና መንፈስ ቅዱስ በውስጣቸው ለሚኖር አማኞች ስለሆነ በራሳቸው የማይችሉትን በመንፈስ ቅዱስ ብርታት ማድረግ ለሚችሉ ሰዎች የተነገረ ነው፡፡
7. በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የምናያቸው የጥበብ ዓይነቶች ሁለት ናቸው፤ እነዚህም ምድራዊና ሰማያዊ ጥበብ ናቸው፡፡ ሰማያዊ ጥበብ በቁ17 ላይ እንደምንመለከተው በንጽህና፣ በሰላም ወዳድነት፣ በታጋሽነት፣ በእሺ ባይነት፣ በምህረት፣ በመልካም ፍሬ፣ ግብዝነትና አድልዎ ባለማሳየት ሲገለጥ፤፤ ምድራዊው ጥበብ ደግሞ በመራርነት፣ በቅንዓትና ራስን በመውደድ ይገለጣል፡፡ ምድራዊ ጥበብ ሌላው ምንጮቹ ሥጋና አጋንንት ናቸው፡፡
8. ያዕቆብ በቁ14-18 ውስጥ የዘረዘራቸው ነገሮች ክርስትያኖች ጥበብ አለኝ ብለው የሚኩራሩበት ነገር እውነትም በእግዚአብሄር ዘንድ ተቀባይነት ያለውና የሚያኮራ ሰማያዊ ጥበብ ነው ወይስ አሳፋሪ ከምድር፣ ከሥጋና ከአጋንንት የሆነ ጥበብ መሆኑን በመመዘን ራሳቸውን የሚመለከቱበት ሚዛን አድርጎ ነው የሰጣቸው፡፡
9. ይህ ምክር ያተኮረው ለሁላችንም ጌታን እናውቃለን በምንል አማኞች ሁሉ ላይ ነው፡፡

# ጥናት ስድስት ያዕ 4፡1-17 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በቅዱሳን መሃል እየተካሄደ ያለው ነገር ጦርነትና ጠብ ሲሆን፤ ለዚህ ክፉ ነገርም ምንጭ አድርጎ ያዕቆብ የሚነግራቸው በውስጣቸው ከሚዋጉ ምኞቶቻቸው እንደሚመነጭ ነው።
2. እነዚህ ሰዎች የሚፈልጉትን ነገር ለማግኘት የሚጠቀሙባቸው መንገዶች፤ መመኘት፣ መግደል፣ በብርቱ መመኘት፣ መጣላት፣ መዋጋት ናቸው። እነዚህን ሁሉ እያደረጉ የማያደርጉት፣ ቢያደርጉት ግን የሚፈልጉትን ነገር ሊቀበሉ የሚችሉበት ነገር ተብሎ የተነገረው እግዚአብሄርን መለመን ወይም ጸሎት ነው። እግዚአብሄርን ለምነው የማይሰጣቸው ምክንያት ለራሳቸው ስጋዊ ደስታ በማሰብ ስለሚለምኑ ነው።
3. ጸሐፊው የዚህን ዓይነት ሃይለኛና ከባድ ቃል ሲጠቀም ለእነዚህ ሰዎች ሊያስተላልፍ የፈለገው መልዕክት፤ ከእግዚአብሄር ጋራ የፍቅር ቃል ኪዳን የገቡና እርሱን በዋነኛነት ለመውደድ ቃል ገብተው፤ ነገር ግን በዚህ ክፍል እንደምናነበው የራሳቸው ፍቅር ያሸነፋቸው፣ የራሳቸውን ምኞት ከእግዚአብሄር በላይ አስቀድመው ስለሚገኙ ያንን ለመውቀስ እንደሆነ አስባለሁ። ያሉት ሁለት አማራጮች፡ አለምን ወዳጅ ማድረግ ወይም ደግሞ የእግዚአብሄርን ወዳጅነት ጠብቆ ለእርሱ ታማኝ በመሆን መኖር ናቸው።
4. በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ስለ እግዚአብሄር ባህርይ መረዳት የምንችለውና እርሱም በዘጸ 34፡14 ላይ የሚያረጋግጥልን እውነት፤ እግዚአብሄር አምላክ እርሱ ቀናተኛ አምላክ እንደሆነና በሁለንተናችን ልንወደውና ልናመልከው የሚገባን እርሱን ብቻ መሆን እንደሚኖርበት በማያወላዳ መንገድ ይናገረናል። አንዲት ሴት ለሁለት ባሎች ሚስት ልትሆን እንደማትችል በዚሁ ረገድ አንድ ሰው ለሁለቱ ሊሆን አይችልም።
5. የዓለምን ወዳጅነት እንቢ አሻፈረኝ ማለት ከባድና አስቸጋሪ ነገር እንደሆነ ቢታወቅም፤ የእግዚአብሄር ቃል በዚህ ቦታ እንደሚነግረን በትህትና ወደ እርሱ ለሚቀርቡት ሁሉ፤ ከእርሱ ጋራ ወዳጅነታቸውን ለማጠንከር የሚችሉበትን ጸጋ እንደሚሰጥ ቃል መግባቱን እናነባለን።
6. ከሰማይ ዲያቢሎስን እንዲጣል ምክንያት የሆነውና የትዕቢት መነሻና ምንጭ እንደሆነ የሚታወቅ ስለሆነ፤ እነዚህ ሰዎችም ትዕቢትን ከዲያቢሎስ ድርጊት ለይተው እንዳያዩት ማለትም ዲያቢሎስን ተቃወሙና አሸነፉ ማለት ለትዕቢትም ሥፍራ እንዳልሰጡት ያመለክታል። ዲያቢሎስን ከመቃወማችን በፊት ልናደርገው የሚገባን ነገር ለእግዚአብሄር ራሳችንን ማስገዛት ነው። ወደ እግዚአብሄር የተጠጋ ሰው እጁን ያነጻል፣ በዓለምና በሁለት ሃሳብ ማለትም በዓለምና በጌታ መሃል አይዋልልም፣ በሃጥያቱ ይጨነቃል፣ ያዝናል፣ ያለቅሳል።
7. የሰጣቸው ማስጠንቀቂያ እርስ በእርሳቸው እንዳይወነጃጀሉ ሲሆን ምክንያቱም ወንድሙን የሚወነጅል ህግ መጠበቁ ሳይሆን በህግ ላይ ፈራጅ ሆኖ እየፈረደ መሆኑና፤ ይህንንም ሲያደርግ የእግዚአብሄርን ቦታ እየወሰደሆነ ሊረዳ ያስፈልጋል ማለት ነው።
8. እነዚህ ቁጥሮች ያተኮሩት ከፊታቸው ላሉት ቀናትና ዘመናት እቅድ ለሚያወጡ ሰዎች ነው። በዘፈቀደ ኑሮን ማበረታታቱ ሳይሆን፤ ስለትዕቢትና ትህትና ከላይ ባሉት ቁጥሮች እንደተናገረው እቅድ ስናወጣም በትዕቢት ነገን መቆጣጠር እንደምንችል እያሰብን ሳይሆን በትህትና መንፈስ ጌታ ቢፈቅድ ማለት እንደሚኖርብን ለማሳሰብ ነው። ነገን ለመኖር አስተማማኝ የሆነ ነገር እንደሌለና በጌታ ቸርነት ብቻ መታመን እንደሚኖርብን እንማራለን።
9. ይህ ክፍል ሃጥያት የሚለው ነገር፤ መልካም የሆነውን ነገር እያወቁ አለማድረግ ሃጥያት እንደሆነ ነው።

# <u>ጥናት ሰባት ያዕ 5፡1-20 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. ሃብታሞቹን የሚናገራቸው ሊደርስባቸው ስላለው መከራ እንዲያለቅሱና ዋይ ዋይ እንዲሉ ነው። አርቆ ሲያይ የእነዚህ ሰዎች ሃብታቸው ሻግቶ፣ ልብሳቸው ብል በልቶት፣ ወርቅና ብራቸውም ሁሉ ዝጎ ነው የሚያየው። እኔ እንደሚገባኝ በፍርድ ቀን ይህ የነበራቸው ሁሉ ምንም የማይረባና ከንቱ መሆኑን ሲገነዘቡ ቁጭትና ሃዘን ውስጣቸውን ይበላቸዋል ማለት ነው።
2. እነዚህ ሰዎች ሃብታቸውን ያከማቹት የሌሎችን ጉልበት በመበዝበዝ፤ ማለትም ለሰሩበት ዋጋ ደሞዛቸውን ባለመክፈል፣ ንጹሐን ሰዎችን በመኮነንና በመግደል ሃብትን ማከማቸት ችለዋል። የነዚህ ሰዎች ሰራተኞች እያደረጉ ያሉት ነገር ወደ እግዚአብሄር መጮህ ነው። እግዚአብሄር ሁልጊዜ ከደካሞችና ከሚገፉት ጋራ እንደሚቆም ነው የምንመለከተው።
3. እየመከራቸው ያለው ጌታ እስኪመጣ ድረስ እንዲታገሱ ነው። ገበሬ መልካም ፍሬን ለማግኘት የፊተኛውንና የኂለኛውን ዝናብ በትዕግሥት እንደሚጠባበቅ፤ እንዲሁም አማኝ መልካም ነገር ስለሚጠብቀው ሊታገስ ያስፈልገዋል ይላቸዋል። ‹‹ጌታ እስኪመጣ›› ቁ7፣ ‹‹የጌታ መምጫ ተቃርቧል›› ቁ8 እና ‹‹ፈራጁ በደጅ ላይ ቆሞአል›› ቁ9
4. የጌታን ነብያት የመከራና የትዕግሥት ምሳሌዎቻችን አድርገን እንድናያቸው ይመክረናል። እንደነዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች የተባረኩ ተደርገው እንደሚቆጠሩ ነው የሚያሳስበን። የኢዮብን መከራና ትዕግሥቱን በመናገር ሊያስተምረን የፈለገው እውነት፤ እርሱ መከራን ከታገሰ በኂላ ጌታ በብዙ እንደባረከው ሁሉ፤ እኛም መከራን በትዕግሥት ካሳለፍን ከጌታ እጅ ልንቀበል ያለው ነገር እንዳለ ሊያስተምረን ነው።
5. ለነዚህ ሰዎች በዚህ ቁጥር ላይ የያዕቆብ ምክር በማናቸውም ነገር እንዳይምሉ ነው።
6. በመጽሐፉ ሁሉ ‹‹ወንድሞች›› እያለ ስለሚጠራቸው ‹‹በእናንተ መሃል›› ሲልም በአማኞች ወይም በቅዱሳን መሃል መሆኑ ይታወቃል። በቅዱሳን መሃል ቢያንስ ቢያንስ ሶስት ዓይነት ሰዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ይናገራል። እነዚህም፤ በመከራ ውስጥ ያሉ፣ የተደሰቱና የታመሙ ይላቸዋል። ይህንን መረዳት ሁሉንም ዓይነት ሰው በአንዳይነት መንፈስ ውስጥ እንዲገኝ እንዳናስገድደው ይረዳናል እላለሁ።
7. ያዕቆብ ይህንን ሲናገር፤ የቤተ ክርስትያን ሽማግሌዎች ካልጸለዩለት አይፈወስም ማለቱ እንዳልሆነ ነው የሚገባኝ፤ ምክንያቱም በዚያው ክፍል ውስጥ ቁ16 ላይ እንድንፈወስ አንዳችን ለሌላችን እንድንጸልይ ይነግረናል። ያዕቆብ በዚህ ክፍል የታመመው ሰው እንዲፈወስ ካስፈለገ ትኩረቱ በሰዎቹ ማንነት ላይ ሳይሆን በጸሎቱ ዓይነት ላይ ነው። ቁ15ትንና 17ትን ማንበብ ይህንን እውነት ያረጋገጣል።
8. በዚህ ቦታ የኤሊያስን ምሳሌ ማስገባት የፈለገበት ምክንያት፤ ጸሎት የተወሰኑ ሰዎች ብቻ የሚለማመዱት ነገር ማንኛውም በክርስቶስ የጸደቀ ሰው በእምነት በእግዚአብሄር ፊት ከቀረበ ታላቅ ነገርን እግዚአብሄር በእርሱ ውስጥ ሊሰራ እንደሚችል ለማስተማር ነው። ኤልያስ ጻድቅ ሰው ነበረ (ቁ16)፣ ኤልያስ እንደኛው ሰው ነበረ (ቁ17)፣ ኤልያስ አጥብቆ ነው የጸለየው (ቁ17)።
9. ማናችንም ብንሆን መጸለይ እንደምንችል፣ ጸሎታችን ደግሞ እንደ ኤልያስ ጸሎት ከልብ የሆነና እምነትን ተሞልተን መጸለይ እንደሚገባን ያስተምረናል።